# ደንብ

**የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ**
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

**ተዛማጅ ሠነዶች:-** ACG, ACG-RA, ACG-RB, ECJ-RA, IOB

**ኃላፊነት የሚመለከታቸው ጽ/ቤቶች:-** የኦፐሬቲንግ ዋና ኦፊሰር ቢሮ፣ የአካዳሚክ ዋና ኦፊሰር፣ የሰው ሃብት ልማት ዋና ኃላፊ ቢሮ፣ የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ፤
Office of the Chief Operating Officer, Office of the Chief Academic Officer, Office of the Chief of Human Resources and Development, Office of School Support and Well-being

## በትምህርት ቤት አገልግሎት ስለሚሰጡ እንስሳት

I. **ዓላማው**

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት ላይ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ለተማሪዎች፣ ለሰራተኞች፣ እና ለጎብኚዎች አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳትን የአጠቃቀም ሥርአት ለመዘርጋት ነው።

II. **ዳራ**

MCPS የአሜሪካውያን የአካል ጉዳተኞች ህግ (ADA) በሚደነግገው መሰረት የአካል ጉዳተኞች በአገልግሎት መስጫ ተቋም፣በት/ቤት ህንፃዎች፣በመማሪያ ክፍሎች፣ ወይም በት/ቤት ተግባራት ውስጥ አገልግሎት ከሚሰጧቸው እንስሳት ጋር እንዲታጀቡ የመፍቀድ ሀላፊነት እንዳለበት ይገነዘባል።እና የአሜሪካውያን የአካል ጉዳተኞች ደንብ የማሻሻያ ህግ 2008።

III. **ትርጉም**

A. አካል ጉዳተኛ ግለሰብ ማለት:-

1. አንድ ወይም ከዚያ በላይ ዋና ዋና የተሟላ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን የሚገድብ የአካል ወይም የአዕምሮ እክል ያለበት ሰው ነው/ነች፣

2. የዚህ አይነት የአካል ጉዳተኝነት/ስንክልና መኖሩ የተመዘገበ ግለሰብ፣ ወይም

3. የዚህ አይነት የአካል ጉዳተኝነት/ስንክልና መኖሩ የሚታወቅ ግለሰብ።

B. አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ፣ ADA ስር እንደተገለጸው፣ ማንኛውም ውሻ ወይም በተወሰኑ ሁኔታዎች የሰለጠነ ድንክዬ ፈረስ፣ የአካል ጉዳተኛ ግለሰብ ስራ ለመስራት ወይም ተግባራትን ለማከናወን በግል እንዲጠቅም ተብሎ የሰለጠነ እንስሳ ማለት ነው። አንድ አገልግሎት ሰጪ እንስሳ እንዲያበረክት የሰለጠነበት ተግባር ከግለሰቡ(ቧ) የአካል ጉዳተኝነት ጋር በቀጥታ የተያያዘ መሆን አለበት። የእንስሳው ብቸኛ ተግባሩ

ማዝናኛ ወይም ስሜታዊ ድጋፍ ለመስጠት ብቻ ከሆነ ADA እንደ አገልግሎት ሰጪ እንስሳ አይቆጠርም።
1

C. በስልጠና ላይ ያለ ውሻ በወቅቱ "አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ" የሚለውን ትርጉም የማያሟላ ነገር ግን በመሰልጠን ላይ የሚገኝ ውሻ ነው። በሥልጠና ላይ የሚገኝ የአገልግሎት ውሻ ውሾችን በአገልግሎት ሰጪነት የሚያሠለጥን እውቅና ባለው ድርጅት ስር የሚመራ በመሆኑ በውሻው ለሚደርሰው ጉዳት አሰልጣኙ ድርጅት ተጠያቂ ነው።

## IV. የአሥራር ዘይቤ

A. የህዝብ አገልግሎት መስጫ፣ ፕሮግራሞች ወ፣ይም ተግባራት ተደራሽነት

የማህበረሰብ አባላት፣ ተማሪዎች፣ እና ሰራተኞች እንዲገኙበት በሚፈቀድላቸው በሁሉም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረቶች ላይ የአካል ጉዳተኞች እንደ አስፈላጊነቱ አገልግሎት ከሚሰጧቸው እንስሶቻቸው ጋር እንዲሆኑ ተፈቅዶላቸዋል።

1. አካል ጉዳተኛ የሆነ(ች) ግለሰብ አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ ወደ MCPS ንብረት ይዞ ሲመጣ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ስለ ግለሰቡ(ቧ) የአካል ጉዳት ምንነት እና መጠን መጠየቅ የለባቸውም፣ ነገር ግን እንስሳው ለአገልግሎት ሰጪነት ብቁ መሆን አለመሆኑን ለማወቅ የሚከተሉትን ሁለት ጥያቄዎች ማድረግ ይችላሉ።

    a) እንስሳው በአካል ጉዳት ምክንያት አስፈላጊ መሆኑን

    b) እንስሳው የሰለጠነው ምን ዓይነት ሥራ ወይም ተግባር እንዲያከናውን እንደሆነ

2. አንድ እንስሳ ለአካል ጉዳተኛ ሰው ተግባራትን ለማከናወን የሰለጠነ መሆኑ ከታወቀ በኋላ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለአካል ጉዳተኛ ግለሰብ ማቅረብ የለባቸውም።

3. አካል ጉዳተኛው(ዋ) ግለሰብ እንስሳው የሰለጠነው ለአገልግሎት ሰጪነት መሆኑን ማረጋገጫ ሰነዶችን እንዲያቀርብ አይጠየቅም/እንድታቀርብ አትጠየቅም።

B. መስፈርቶች

1. እንስሳው ውሻ ወይም በአንዳንድ ሁኔታ ትንሽ ፈረስ መሆን አለበት።

2. እንስሳው ለአካል ጉዳተኛው(ዋ) ግለሰብ ሥራ ለመሥራት ወይም ተግባር ለማከናወን በግለሰብ ደረጃ የሰለጠነ መሆን አለበት።

3. አገልግሎት ሰጪው እንስሳ በባለቤቱ ቁጥጥር ስር መሆን አለበት። አገልግሎት ሰጪ እንስሳ ልጓም፣ ማሰሪያ ወይም ሌላ ማገጃ ሊኖረው ይገባል፣ ወይም ባለቤቱ ልጓም፣ ማሰሪያ ወይም ሌላ ማገጃ ለመያዝ የማይችል/የማትችል ጉዳተኛ ከሆነ(ች) የአገልግሎት የሚሰጠው እንስሳ ደህንነቱ

---

a) የቴራፒ ውሾች በፌደራል ህግ በህጋዊነተ ለዚህ ዓላማ በአገልግሎተ ሰጪነት ስላልተመዘገቡ ADA ስር የህዝብ መዳረሻዎች ላይ መገኘት አይችሉም። ከባለቤቶቻቸው ውጭ ለሆኑ ሰዎች የቴራፕዩቲክ ግንኙነት ይሰጣሉ እንጂ የአገልግሎት ሰጪ እንስሳነትን ምደባ መስፈርቶችን አያሟሉም።

b) የቴራፒ ውሾች በፌደራል ህግ በህጋዊነተ ለዚህ ዓላማ በአገልግሎተ ሰጪነት ስላልተመዘገቡ ADA ስር የህዝብ መዳረሻዎች ላይ መገኘት አይችሉም። ከባለቤቶቻቸው ውጭ ለሆኑ ሰዎች የቴራፕዩቲክ ግንኙነት ይሰጣሉ እንጂ የአገልግሎት ሰጪ እንስሳነትን ምደባ መስፈርቶችን አያሟሉም።

c) የቴራፒ ውሾች በፌደራል ህግ በህጋዊነተ ለዚህ ዓላማ በአገልግሎተ ሰጪነት ስላልተመዘገቡ ADA ስር የህዝብ መዳረሻዎች ላይ መገኘት አይችሉም። ከባለቤቶቻቸው ውጭ ለሆኑ ሰዎች የቴራፕዩቲክ ግንኙነት ይሰጣሉ እንጂ የአገልግሎት ሰጪ እንስሳነትን ምደባ መስፈርቶችን አያሟሉም።

የተጠበቀ፣ ውጤታማ የስራ ወይም የእንስሳውን የተግባር አፈጻጸም የሚያደናቅፍ ከሆነ፣ አገልግሎት ሰጪው እንስሳ በባለቤትየው ቁጥጥር ስር መሆን አለበት (ለምሳሌ፡- በድምጽ ቁጥጥር ማድረግ፣ በምልክት/በሲግናል ወይም ሌሎች ውጤታማ መንገዶችን መጠቀም ያስፈልጋል)።

4. MCPS ለማንኛውም የአገልግሎት ሰጪ እንስሳ እንክብካቤ ወይም ክትትል ኃላፊነት የለበትም።

C. ትናንሽ ፈረሶች

1. ትንሽ ፈረስ በአገልግሎት ሰጪነት ወደ አንድ የተለየ ፋሲሊቲ መግባት ይችል እንደሆነ ለመገምገም የሚከተሉት ሁኔታዎች ግምት ውስጥ መግባት አለባቸው፡-

    a) ትንሽ ፈረስ አይነቱ፣ መጠኑ እና ክብደቱ እና ፋሲሊቲው እነዚህን ሁኔታዎች መሸከም እና እንስሳው አገልግሎቱን መስጠት ይችል እንደሆነ ማረጋገጥ፤

    b) ተጠቃሚው(ዋ) ትንሽ ፈረስ ላይ በቂ ቁጥጥር ማድረግ ይችል እንደሆነ ማረጋገጥ፤

    c) ትንሹ ፈረስ ቤት ውስጥ አገልግሎት መስጠት ይችል እንደሆነ ማወቅ፤ እና

    d) ትንሹ ፈረስ በፋሲሊቲው ውስጥ መገኘቱ ለስራ ደህንነት አስፈላጊ የሆኑ መስፈርቶችን የሚጥስ መሆን/አለመሆኑን ማረጋገጥ።

2. ይህ ደንብ ሰክሽን I እስከ IV ስር በተገለጹት ትንንሽ ፈረሶችም ላይ ይሠራል።

D. ሰራተኞች ወይም ተማሪዎች ለሚያስፈልጓቸው የአገልግሎት እንስሳት ዝግጅት ማድረግ

1. የሰው ሃብት ልማት ጽህፈት ቤት ለአገልግሎት እንስሳት ADA መቆያለሚፈልጉ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ማቆያ እና ሰራተኞች ለሚያስፈልጋቸው የአገልግሎት እንስሳት የቦታ ዝግጅት የማድረግ ሃላፊነት አለበት።

2. ADA አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳትን ለሚፈልጉ ተማሪዎች እና ወላጆች/አሳዳጊዎች የልዩ ትምህርት ጽሕፈት ቤት (OSE) ሪሶርስ ስለሆነ ወላጆችን/አሳዳጊዎች፣ተማሪዎች፣ እና ትምህርት ቤቶችን ለሚፈለጉት አይነት የአገልግሎት እንስሳት የሚያገኙበትን ሁኔታ የማዘጋጀትና የመርዳት ኃላፊነት አለበት። OSE የመፍትሔ እና አስፈጻሚ ክፍል ለተማሪዎች አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳትን ማዘጋጀት በሚመለከት ለትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች ድጋፍ ይሰጣል።

3. የአገልግሎት እንስሳትን የሚጠቀሙ ብቁ ተማሪዎች እና የአገልግሎት እንስሳትን የሚጠቀሙ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች ከት/ቤት ሰራተኞች ጋር በንቃት መተባበር እና በትምህርት ቤት የአገልግሎት እንስሳት የሚያገኙበትን ዝግጅት መደረግ አለበት። ዝግጅት ለማድረግ እንደ አስፈላጊነቱ ከግምት ውስጥ ሊገቡ የሚችሉ ምሳሌዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

    a) አገልግሎት የሚሰጡ እንስሳት የሚቆዩበት ቦታ እና የሚያርፉበት ጊዜ

    b) አገልግሎት የሚሰጠው እንስሳ ራሱን ለማናፈስ ተስማሚ ቦታ እና ሰዓት።

    c) እንደአስፈላጊነቱ ስለ አገልግሎት ሰጪው እንስሳ ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች መረጃ።

    d) እንደ አስፈላጊነቱ ስለ አደጋ ጊዜ ሂደቶች መግለጫ።

4. አካል ጉዳተኛ ግለሰቦች፣ ሰራተኞች ወይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ አገልግሎት የሚሰጡት እንስሳት አገልግሎት ለመስጠት የሚያስፈልጋቸውን ቁሳቁሶችን እና መሳሪያዎችን የማቅረብ ሃላፊነት አለባቸው።

E. እንክብካቤ እና ተጠያቂነት

1. የአገልግሎት ሰጪ እንስሳት ባለቤቶች እንስሳቱ በሌሎች ተማሪዎች፣ በሰራተኞች፣ በጎብኝዎች እና/ወይም በንብረቶች ላይ ለሚያደርሱት ጉዳት ተጠያቂ ናቸው።

2. አገልግሎት ሰጪ እንስሳት ያላቸው ተማሪዎች እንስሳቸውን መቆጣጠር እና መንከባከብ ይጠበቅባቸዋል። አገልግሎት የሚሰጠውን እንስሳ መቆጣጠር ወይም መንከባከብ የማይችል ትንሽ ልጅ ወይም አካል ጉዳተኛ ተማሪ ከሆነ(ች) ወላጅ/አሳዳጊ እንስሳውን የመንከባከብ እና የመቆጣጠር ሃላፊነት አለበት። ከአገልግሎት ሰጪ እንስሳት እንክብካቤ እና ቁጥጥር ጋር የተያያዙ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በህንፃው አስተዳዳሪ ውሳኔ መሰረት ምላሽ ያገኛሉ።

F. አገልግሎት የሚሰጥ እንስሳ ማስወገድ ወይም መከልከል

ከሚከተሉት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ ከተከሰተ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የአካል ጉዳተኛ ግለሰብን ወይም የአካል ጉዳተኛ ተማሪ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን አገልግሎት የሚሰጠው እንስሳ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት እንዲወገድ ሊጠይቅ ይችላል።

1. እንስሳው ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ እና የእንስሳው ተገልጋይ ባለቤት ለመቆጣጠር ውጤታማ እርምጃ መውሰድ ካልቻለ።

2. እንስሳው ቤት ውስጥ ለማዳ ካልሆነ ወይም የእንስሳው ተቆጣጣሪ አገልግሎት ሰጪ እንስሳውን እንስሳ ለማናፈስ የተሰየሙ ቦታዎችን እና ጊዜውን ቸል የሚል ከሆነ።

3. የእንስሳው መገኘት አገልግሎቱን፣ ፕሮግራሙን ወይም እንቅስቃሴውን የሚያደናቅፍ ከሆነ።

4. እንስሳው በትክክል ከተወገደ፣MCPS ለአካል ጉዳተኛው(ዋ) በአገልግሎቱ፣ በፕሮግራሙ ወይም በእንቅስቃሴው ውስጥ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ በማመቻቸት እድል ይሰጣል።

G. በስልጠና ላይ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ እንስሳት

1. MCPS ከዚህ በታች በተገለጹት ሁኔታዎች በስልጠና ላይ የሚገኙ አገልግሎት የሚሰጡ ውሾች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ እንዲገቡ/እንዲገኙ ይፈቅዳል። ስልጠናው የትምህርት ቤቱን የትምህርት ሂደት የማያደናቅፍ ወይም ጣልቃ የማይገባ ከሆነ። በመደበኛነት በመማሪያ ክፍል ውስጥ በትምህርት ጊዜ ስልጠና ይካሄዳል ተብሎ አይጠበቅም።

2. በማንኛውም ጊዜ በአንድ ትምህርት ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የአገልግሎት ውሻ ስልጠና መስጠት አይፈቀድም።

3. በስልጠና ላይ የአገልግሎት ውሻ ባለቤት የሆነው ድርጅት የሚከተሉትን ማቅረብ አለበት፦

   a) የክትባት ሰነድ፣ የተጠያቂነት ኢንሹራንስ ዋስትና ማረጋገጫ፣ እና ውሻው ቤት ለማዳ እና ቢያንስ ስድስት ወር እድሜ ያለው መሆኑን ማረጋገጫዎች ያስፈልጋሉ።

b) ከላይ በሰክሽን IV.D.3 የተዘረዘሩ ዝግጅቶችን ጨምሮ ውሻው በትምህርት ቤት እንዴት እንደሚያዝ የሚገልጽ ለርእሰ መምህሩ የቀረበ እቅድ።

c) እንስሳው በስልጠና ላይ ያለ አገልግሎት ሰጪ ውሻ መሆኑን የሚለይ ማገጃ፣ ቬስት ወይም ሌላ ተገቢ መሳሪያ ውሻው በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ላይ እያለ በማንኛውም ጊዜ ሊደረግለት ይገባል።

4. ከላይ በሰክሽን IV.F እንደተገለፀው በስልጠና ላይ ያለ የአገልግሎት ውሻ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ሊወገድ ይችላል።

5. በትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር ውሳኔ MCPS ከድርጅቱ ባለ ሶስት ክፍል የአገልግሎት ሰጪ ቡድን አካል የሆነ ውሻ በአሰልጣኝ አማካይነት MCPS ትምህርት ቤት ውስጥ ስልጠና ሊሰጥ፣ እና ከት/ቤት ሥራ ጋር ለተያያዘ ተግባር ወይም እንቅስቃሴ በት/ቤት ንብረት ላይ የአግልግሎት ውሻ ስልጠና ማካሄድ ይቻላል።

**ተዛማጅ የመረጃ ምንጮች፦** 1990 የአካል ጉዳተኞች አሜሪካውያን ህግ (ADA)፣ የአካል ጉዳተኞች አሜሪካውያን ደንብ ማሻሻያ ህግ 2008 (ADAAA)፤ የፌደራል ደንቦች ኮድ፣ Title 28፤ §35.104፤ §35.130(b)(7) እና §35.136

**የደንቡ ታሪክ፦** አዲስ ደንብ፣ ጁላይ 24, 2013፤ ሜይ 16, 2014 ተሻሽሏል፣ ጃኑዋሪ 26, 2024 ተሻሽሏል።

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መግለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ማድረግን ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (ግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም ህገ-መንግሥታዊ ጥበቃ የተደረገላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፣ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትኃዊነት፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለማስፈን እና ለማዳበር/ለመንከባከብ ሲካሄድ የቆየውን ጥረት ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምድ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ "የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ ACA" ይመልከቱ፡- "ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን  እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ለሴት ልጆች በስካውትነት እና በሌሎች የወጣት ቡድኖች ለመመደብ እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።

A. በሜሪላንድ ስቴት ፖሊሲ መሠረት ሁሉም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና የትምህርት ቤት ፕሮግራሞች የሚከተሉትን ድንጋጌዎች በማክበር መንቀሳቀስ አለባቸው፡-
   (1) 1964 የፌደራል ሲቪል መብቶች ህግ አንቀጽ VI፣ እና
   (2) በሜሪላንድ ኮድ የትምህርት ደንብ አንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 7፣ ይኼውም የህዝብ እና በህዝብ የገንዘብ ድጋፍ የሚደረግላቸው ትምህርት ቤቶች እና ፕሮግራሞች፡-
      (a) በዘር፣ በጎሳ፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በጾታ፣ በእድሜ፣ በብሔር፣ በጋብቻ ሁኔታ፣ በፆታዊ ሁኔታ፣ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት፣ ወይም የአካል ጉዳተኝነት ምክንያት፣ አሁን ባሉት ተማሪዎች ላይ፣ የወደፊት ተማሪዎች ላይ፣ ወይም የአሁን ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች ላይ አድልዎ ማድረግ የተከለከለ ነው፣
      (b) በአንድ ግለሰብ ዘር፣ ጎሳ፣ ቀለም፣ ምክንያት የወደፊት ተማሪዎችን መመዝገብ እምቢ ማለት፣ የአሁኑን ተማሪዎች ማባረር፣ ወይም ከአሁን ተማሪዎች፣ የወደፊት ተማሪዎች ወይም የአሁኑ ወይም የወደፊት ተማሪዎች ወላጆችን ወይም አሳዳጊዎችን የሃይማኖት፣ የጾታ፣ የዕድሜ፣ የብሔር፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የፆታ ዝንባሌ፣ የፆታ ማንነት ወይም የአካል ጉዳት፣ የመሳሰሉትን ምክንያት በማድረግ መብቶችን መከልከል፣ ወይም
      (c) የትምህርት ውጤቱ(ቷ) ምንም ይሁን ምን መርሃ ግብሩ ወይም ትምህርት ቤቱ በተማሪው(ዋ) ላይ አድሎአዊነትን ፈጽመዋል የሚል ቅሬታ ባቀረበ(ች) ተማሪ ወይም ወላጅ ወይም አሳዳጊ ላይ ቅጣት ማድረግ፣ ወይም ማንኛውንም ሌላ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው**

እባክዎን የግንኙነት መረጃ እና የፌዴራል፣ የስቴት፣ ወይም የአካባቢ መረጃ ይዘትን በተመለከተ መስፈርቶቹ በዚህ ሰነድ እትም ላይ ተለውጠው ሊሆን ይችላል፥እና በወቅታዊ መረጃ እንደተተካ ልብ ይበሉ።  በዚህ ውስጥ የተካተቱትን መግለጫዎች እና ማመሳከሪያዎችን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት እባክዎን ይህንን በይነመረብ ይመልከቱ፡- www.montgomeryschoolsmd.org/info/nondiscrimination

| በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች ላይ ስለሚደርስ መድልዎ ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| 1973 የተሃድሶ ድእንብ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የመገልገያ/አኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የመገልገያ/የአኮሞዴሽን/ጥያቄ ማቅረቢያ አድራሻ ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡- |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning, and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630 \| 504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888 \| DCI@mcpsmd.org |
| ታይትል IX ስር ስለ ፆታዊ መድልዎ፣ ጾታዊ ትንኮሳን ጨምሮ፣ በተማሪዎች ላይ ወይም በሰራተኞች ላይ ስለሚደረግ ጥቃት ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ አድራሻው ከዚህ በታች የሚገኘው ነው፡-*** | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>15 West Gude Drive, Suite 200, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215 \| TitleIX@mcpsmd.org | |

*ይህ መግለጫ ከተሻሻለው የፌዴራል የአንደኛ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ህግ ጋር የተጣለጠ ነው።

**ይህ መግለጫ የሜሪላንድ ዝርዝር ደንብ/ኮድ አንቀጽ 13A.01.07. ጋር የተጣለጠ ነው።

***የመድሎአዊነት ቅሬታዎችን ለሚከተሉት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡-

U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY);  Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; Agency Equity Officer, Office of Equity Assurance and Compliance, Office of the Deputy State Superintendent of Operations, Maryland State Department of Education, 200 West Baltimore Street, Baltimore, MD 21201-2595, oeac.msde@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, ወይም www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቋንቋ/ፎርማት ማግኘት ካስፈለገ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay) ወይም PIO@mcpsmd.org በመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤትን በዚህ ኤሜይል ወይም በስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services ስልክ ቁጥር 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, oወይም MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

ፌብሩዋሪ 2024